7ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

## 1. የዲሞክራሲ ሥርዓት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 13**

- የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ተግባራት ያውቃሉ፡፡
- የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረታዊ መርሆዎችን ያውቃሉ፡፡
- የመንግሥት የሥልጣን አካላትን አወቃቀር ይገነዘባሉ፡፡
- ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ የመኖር ጠቀሜታን ይረዳሉ፡፡

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • መሠረታዊ የዴሞክራሲ ሥርዓት መርሆችን ያብራራሉ፣ | 1.1 የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆች፣(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.1.1 ነፃ የፖለቲካ ሥልጣን ውድድር፣<br>1.1.2 የህግ የበላይነት፣<br>1.1.3 ግልጽነትና ተጠያቂነት፣<br>1.1.4 የብዙሀን ድምፅ የበላይነት እና የአነስተኛው ድምፅ መከበር፣ | • ተማሪዎቹ የዴሞክራሲ መሠረታዊ መርሆችን ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ እንዲያብራሩ ማድረግ፡፡ ካላወቁ በይዘትነት የተጠቀሱትን መሠረታዊ መርሆች ማሳወቅና በእያንዳንዱ መርሆ ላይ የክፍሉ ተማሪዎች እንዲወያዩበት በማድረግ ትምህርቱን በደንብ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን መስጠት፡፡ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የግለሰብና የቡድን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ይዘረዝራሉ፣ | 1.2 ሰብዓዊና ዴሞክራሲያ መብቶች፣ **(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.2.1 የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶች፣<br>- በሕይወት የመኖር መብት፣<br>- በአካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ መብት፣<br>- ከሕግ ውጪ ያለመያዝ፣ ያለመከሰስና ያለመታሰር መብት፣<br>1.2.2 የቡድን ሰብዓዊ መብቶች፣<br>- የእኩልነት መብት፣<br>- የሃይማኖትና የእምነት ነፃነት፣<br>1.2.3 የግለሰብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣<br>- ማንኛውንም አመለካከት የማራመድና ሀሳብን በነፃ የመግለጽ መብት፣<br>- የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና አቤቱታ የማቅረብ መብት፣<br>- የመደራጀት መብትና የመዘዋወር ነፃነት፣<br>1.2.4 የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣<br>- የሕዝብ ሉዓላዊነት፣<br>- የብሔሮች ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደ መብት፣ | • ሁለት ቡድኖችን በማዘጋጀት አንዱ ቡድን በፌዴራል ሕገመንግሥት የተጠቀሱትን የዴሞክራሲያዊ መብቶች፣ ሌላኛው ደግሞ የሰብዓዊ መብቶችን ዝርዝር እንዲያዘጋጁና ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡ ማድረግ። በክፍል ውይይታቸውም በሁለቱም መብቶች የግለሰብና የቡድን መብቶች ተለይተው በተማሪዎች እንዲታወቁ ውይይቱን ወደዚሁ አቅጣጫ መምራት ተገቢ ይሆናል።<br>• በተለይ የቡድን ዴሞክራሲያዊ መብቶችን በተመለከተ የኢትዮ ጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እራሳቸውን የማስተዳደር መብት እውቅና የተሰጠው እንደመሆኑ ተማሪዎች በዚህ ላይ እንዲወያዩና የዚህንም ጠቀሜታ ለክፍል ሪፖርት እንዲያደርጉ ማስቻል። |
| • ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣ | 1.3 ልዩነቶችን ማቻቻል፣**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>1.3.1 ልዩነቶችን ማቻቻል አብሮ ለመኖር ያለው ጠቀሜታ፣<br>- ለግለሰብ፣<br>- ለቤተሰብ፣<br>- ለሕብረተሰብ፣ | • እንደሚታወቀው ሕይወት በልዩነት የተሞላች ናት። በክፍል ውስጥ እንኳን የተለያዩ ልዩነቶች ይታያሉ። በመጀመሪያ ተማሪዎች በክፍላቸው ውስጥ የሚታያቸውን ልዩነቶች እንዲገልጹ ማድረግ። በማስከተልም በቤተሰብ ደረጃ የሚያውቋቸውን ልዩነቶች እንዲያብራሩ ማድረግ። ከዚያም በአካባቢያቸው ደረጃ የሚረዱቸውን ልዩነቶች እንዲተነትኑ ማድረግ።<br>• ልዩነቶች መኖራቸው ላይ ስምምነት ከተደረሰ በኋላ እነዚህ ልዩነቶች |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | እንደተጠበቁ ሁነው እንዴት በሰላም አብሮ መኖር እንደሚቻልና በሰላም አብሮ መኖርም ለነሱ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸውና ለሕብረተሰባቸው የሚሰጠውን ጥቅም በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና ለክፍል ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ። |
| • የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ተግባራትን ያብራራሉ፣ | 1.4 የመንግሥት ተግባራት፣(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.4.1 የኢትዮጵያ የፌዴራል መንግሥት ተግባራት፣<br>1.4.1 የክልል ብሔራዊ መንግሥታት ተግባራት፣<br>1.4.3 የከተማ አስተዳደርና ተጠሪነት፣ | • ተማሪዎቹን በሁለት ቡድን በመክፈል አንዱ ቡድን በፌዴራል ሕገመንግሥት እንዲሁም በክልል ሕገመንግሥት መሠረት ክልላቸው የሚያከናውናቸውን ተግባራት፣ ሁለተኛው ቡድን ደግሞ የፌዴራል መንግሥት የሚያከናወናቸው ተግባራትን በመለየት ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡ በማድረግ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የመንግሥት የሥልጣን አካላትን ይዘረዝራሉ፣ | 1.5 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የሥልጣን አካላት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.5.1 ሕግ አውጪ፣<br>1.5.2 ሕግ አስፈጻሚ፣<br>1.5.3 ሕግ ተርጓሚ፣ | • ሥልጣን በአንድ ቦታ ላይ መማከሉን ለመከላከል የመንግሥት ሥልጣን በሦስት ቦታ እንዲከፋፈል ተደርጓል። ይህም አንዱ የሥልጣን አካል ሌላውን እንዲቆጣጠር ለማስቻል ይረዳል። ተማሪዎች የእያንዳንዱን አካል ተግባር በደንብ እንዲያውቁ ከተደረገ በኋላ ይህ ዐይነት የመንግሥት አደረጃጀት የሚሰጠውን ጠቀሜታ ተወያይተው በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ይገልፃሉ፣ | 1.6 የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት፣(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>1.6.1 ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ያደረገችው አስተዋጽኦ፣<br>- የአፍሪካን የነፃነት ትግል ማገዝ፣<br>- ሰላምን ማስከበር፣ | • ኢትዮጵያ ነፃነቷን ጠብቃ የቆየች ሀገር ከመሆኗ ባሻገር በቅኝ አገዛዝ ሲማቀቁ ለነበሩ የአፍሪካ ሀገራት ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ በርካታ ድጋፎችን ያደረገች ነች። ከዚያም ባሻገር በአፍሪካ ውስጥ ሰላም በሚደፈርስበት ጊዜ የኢትዮጵያ ሠራዊት በቦታው እየተገኘ የሰላም ማስከበር ኃላፊነቱን ተወጥቷል። ተማሪዎች እነዚህን ድጋፎች በደንብ እንዲረዱቸው ከተደረገ በኋላ የኢትዮጵያ የውጪ ግንኙነት እዚህ ላይ ማተኮሩ በወቅቱ ለአፍሪካ የሰጠውን ጥቅም በተመለከተ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

# ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** መሠረታዊ የዴሞክራሲ ሥርዓት መርሆችን ይዘረዝራሉ፣የግለሰብና የቡድን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ይዘረዝራሉ፣ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ተግባራትን ያብራራሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ተግባራትን ይለያሉ፣የመንግሥት የሥልጣን አካላትን ይዘረዝራሉ፣ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** መሠረታዊ የዴሞክራሲ ሥርዓት መርሆችን ያብራራሉ፣የግለሰብና የቡድን ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ይዘረዝራሉ፣ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ተግባራትን ያብራራሉ፣የፌዴራልና የክልል መንግሥታት ተግባራትን ያብራራሉ፣የመንግሥት የሥልጣን አካላትን ይዘረዝራሉ፣ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ያደረገችውን አስተዋጽኦ ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 2. የሕግ የበላይነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 10**

- የሕገመንግሥትንና የሌሎች ህጐችን ምንነት ያውቃሉ።
- የሕግ ከለላ መገለጫዎችንና ያለውንም ጠቀሜታ ያውቃሉ።
- የመንግሥትና የሕዝብ ተመራጮች ሥልጣናቸው በህግ የተገደበ መሆኑን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የፌዴራል ሕገ መንግሥትን ምንነትና አስፈላጊነት ያብራራሉ፣ | 2.1 ሕገመንግሥት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.1.1 የፌዴራል ሕገመንግሥት ምንነት፣<br>2.1.2 የፌዴራል ሕገመንግሥት አስፈላጊነት፣<br>2.1.3 የሕግ ከለላ ለዜጐች የሚሰጠው ጥቅም፣ | • በዚህ ደረጃ ላይ ተማሪዎቹ አጠቃላይ የሆነ የሕገመንግሥት መሠረታዊ ሀሳብ እንደሚኖራቸው ይገመታል። እዚህ ላይ እንዲያውቁት የሚፈለገው ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የፌዴራል ሕገመንግሥቱን ምንነትና አስፈላጊነት ነው። ለአብነት ያህልም የፌዴራል ሕገመንግሥቱ የህጐች ሁሉ የበለላይ ህግ ሲሆን፤ በሀገሪቱ የፌዴራል ሥርዓት እንዲኖር ያስቻለ ነው። አስፈላጊነቱ የሚመነጨውም ለኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እውቅና የሰጠና ክልላቸውን እንዲያስተዳድሩ ያስቻለ በመሆኑ የሀገሪቱ ዜጐች በመፈቃቀድ ላይ በተመሠረተ በሰላም አብረው እንዲኖሩ የሚያደርግ ስለሆነ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ተማሪዎቹ በጥልቀት ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • እንደ ሕብረተሰብ አባልነታቸው ከነሱ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይገልፃሉ፣<br>• በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን መልካም ሥነምግባሮች ይላበሳሉ፣ | 2.2 ሥነምግባር፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>2.2.1 ሕብረተሰቡ ከተማሪዎች የሚጠብቀው ሥነምግባር፣<br>- የሕብረተሰቡን አባላት ማክበር፣<br>- የሕብረተሰቡን በጐ ምግባሮች (ዕሴቶች) ማክበር፣<br>- የሕብረተሰቡን ችግሮች ለማስወገድ አቅም | • ሥነምግባርን እንዲከልሱ ከተደረገ በኋላ ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል እንደ ሕብረተሰብ አባልነታቸው የሚጠበቅባቸው ሥነምግባር ምን እንደሆነ እንዲወያዩባቸው ማድረግ። ይህን የቡድን ውይይት በክፍል ውይይት በማጠናከር ተማሪዎቹ መልካም ሥነምግባርን እንዴት ማጐልበት እንደሚችሉ እንዲወያዩበት ማድረግ፣ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | የፈቀደውን ሁሉ ማድረግ፣ | |
| • የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣ | 2.3 የሥልጣን ገደብ፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.3.1 በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ የሥልጣን ገደብ የመጣል አስፈላጊነት፣ | • ምንጊዜም ሥልጣን ገደብ ካልተጣለበት ከሥልጣን ውጪ መጠቀምን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ወረዳ አስተዳዳሪ የፈለገውን ማድረግ የሚችል ከሆነ ሕብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ በደል ሊፈፅም ይችላል፡፡ በደሉንም የሚፈፅመው አውቆና ውጤቱን ፈልጐ ወይንም ባለማወቅ ሥልጣን ስላለው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ሥልጣንን መገደብ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎቹ በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲወያዩና የሥልጣን ገደብ መኖር ተገቢ መሆኑ ላይ በራሳቸው ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡ |
| • የቤተሰብ ሚስጥር ምንነት ይገልፃሉ፣<br>• የቤተሰብን ሚስጥር አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ያብራራሉ፣ | 2.4 ሚስጥር፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.4.1 የቤተሰብ ሚስጥር፣<br>2.4.2 የቤተሰብን ሚስጥር አለመጠበቅ የሚያስከትለው ጉዳት፣ | • የሚስጥር ዓይነቶች ከሆኑት ውስጥ አንዱ የቤተሰብ ሚስጥር ነው፡፡ የቤተሰብ ሚስጥርን አለመጠበቅ ለቤተሰቡ የተለያዩ ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል፡፡ የቤተሰብ ሚስጥር ናቸው የሚሏቸውን ተማሪዎቹ እንዲዘረዝሯቸው ማድረግ፡፡<br>• እነዚህን ሚስጥሮች አለመጠበቅ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳቶችን ተማሪዎቹ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩባቸው ማድረግና የቤተሰብን ሚስጥር መጠበቅ ተገቢነት ላይ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፡፡ |
| | 2.5 ሙስና (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>2.5.1 ሙስና በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ፣ | • የሙስናን አስከፊነት እንዲከልሱት ማድረግ፡፡ ለዚህም እንዲረዳ ሙስናን ተማሪዎቹ እንዴት እንደሚገነዘቡት እንዲገልፁ ማድረግ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል መንግ ሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ የአካባቢ ተቋማት የሙስና ተግባ ራት እንዴት እንደሚፈፀሙ እንዲወያዩባቸውና በአጠቃላይ ውይይት የጋራ አመለካከት እንዲይዙ ማድረግ፡፡ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፌዴራል ሕገ መንግሥትን ምንነትና አስፈላጊነት ይለያሉ፣እንደ ሕብረተሰብ አባልነታቸው ከነሱ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይዘረዝራሉ፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን መልካም ሥነምግባሮች ይዘረዝራሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትንይለያሉ፣የቤተሰብ ሚስጥር ምንነት ይዘረዝራሉ፣የቤተሰብን ሚስጥር አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፌዴራል ሕገ መንግሥትን ምንነትና አስፈላጊነት ያብራራሉ፣እንደ ሕብረተሰብ አባልነታቸው ከነሱ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይገልፃሉ፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን መልካም ሥነምግባሮች ይላበሳሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የቤተሰብ ሚስጥር ምንነት ይገልፃሉ፣የቤተሰብን ሚስጥር አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ያብራራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

**3. እኩልነት**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8**

- የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች ለይተው ያውቃሉ።
- ሴቶችና ወንዶች በማንኛውም ሁኔታ እኩል መሆናቸውን ይረዳሉ።
- የአካል ጉዳተኞችን የእኩል ተጠቃሚነት መብቶች ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • በኢትዮጵያ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች የማረጋገጫ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣ | 3.1 የእኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.1.1 የብሔሮችr የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች መገለጫዎች፣ | • በኢትዮጵያ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች በሕገመንግሥት ተረጋግጧል። የዚህ መገለጫ ከሆኑት ውስጥ ለምሳሌ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ መደረጉ ተጠቃሽ ነው። ስለሆነም ተማሪዎቹ ተከፋፍለው የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ሕገመንግሥቶች በማገናዘብ በኢትዮጵያ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የህዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች የተረጋገጡባቸውን መገለጫዎች እየነቀሱ በማውጣት እንዲወያዩበቸውና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የብሔሮች፣ ብሔረሰቦ ችና ህዝቦች ቋንቋዎች ሃይማኖቶችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እኩልነት መከበር አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣<br>• በደረጃቸው እነዚህን እኩልነቶች የሚፃረሩ ሁኔታዎችን ይታገላሉ፣ | 3.1 የብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቋንቋዎችና የሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እኩልነት መከበር አስፈላጊነት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>- ለዘላቂ ሰላም፣<br>- ፈጣን ልማትንና እድገትን ለማረጋገጥ፣ | • በመጀመሪያ ተማሪዎች ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መኖሪያ ሀገር መሆኗን እንዲረዱና በዚህ ላይ መግባባት መኖሩን ማረጋገጥ። በማስከተለም የነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብቶች ካልተከበሩ በሀገሪቱ አለመረጋጋትና ብጥብጥ ሊነግስ የሚችል ሲሆን፤ በተቃራኒው መብታቸው ከተከበረ ደግሞ ልማትና እድገት ሊፋጠን ይችላል።<br>• ስለሆነም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብታቸው ካልተከበረ ሊከተል የሚችለውን ጉዳት፤ ከተከበረ ደግሞ ሊገኝ የሚችለውን ብልፅግና አስመልክቶ እንዲወያዩና ይህን ውይይትም በአጠቃላይ የክፍል ውይይት በማጠናከር የጋራ ድምዳሜ ላይ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ሴቶች በትዳራቸውና በቤተሰብ ኑሮ ውስጥ ያላቸውን የእኩልነት መብት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• በቤተሰባቸውና በአካባቢያቸው የሴቶችን የእኩልነት መብቶች ያከብራሉ፣ | 3.3 የፆታ እኩልነት፣<br>**(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.3.1 የሴቶች የእኩልነት መብት፣<br>3.3.2 የሴቶች የእኩልነት መብት መገለጫዎች፣ | • ትምህርቱን ለመጀመር እያንዳንዱ ተማሪ «ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ናቸው » በሚለው ጽንሰ ሀሳብ ላይ የግል አስተያየቱን እንዲሰብና ይህ እኩልነት እንዴት እንደሚገለጽ እንዲያብራራ ማድረግ። በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ሴቶች እንዴት የትዳር ጓደኛቸውን መምረጥ እንደሚገባቸውና ትዳር ከመሠረቱም በኋላ ከባላቸው ጋር ሊኖራቸው የሚገቡ መብቶች ምን ዓይነት ደረጃ መያዝ እንዳለባቸው ውይይት በማድረግ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የአካል ጉዳተኞች መብቶች አለመከበራቸው ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳቶችን ይገልፃሉ፣ | 3.4 የአካል ጉዳተኞች መብቶች፣<br>**(1 ክፍለ ጊዜ)**<br>3.4.1 የአካል ጉዳተኞች መብት አለመከበር የሚያስከትለው ጉዳት፣ | • የኢትዮጵያ አድገትና ብልፅግና ይፋጠን ዘንድ ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ይገባዋል። የኢትዮጵያ ዜጐች ከሆኑት ውስጥም አካል ጉዳተኞች ይገኙበታል። አካል ጉዳተኞች እንደማንኛውም ዜጋ መብቶቻቸው ከተከበሩና በቂ እገዛ ከተደረገላቸው ደግሞ ለሀገር የሚጠቅም ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚችሉ በተግባር አሳይተዋል።<br>• ስለሆነም ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የአካል ጉዳተኞች መብቶችን አለመከበር ሊያስከትለው የሚችለው ጉዳት ላይ እንዲወያዩና የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ። |
| • የሃይማኖት ዕኩልነት መከበር ያለውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ። | 3.5 የሃይማኖት ዕኩልነት መከበር ያለው ጠቀሜታ<br>**(1 ክፍለ ጊዜ)** | • በአካባቢያቸው የሚገኙ የተለያዩ ሃይማኖቶችን እንዲጠቅሱ በማድረግ የሃይማኖቶቹ ዕኩልነት መከበር የሚኖረውን ጠቀሜታ እንዲናገሩ ማድረግ፣ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በኢትዮጵያ የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች የማረጋገጫ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፣የብሔሮች፣ ብሔረሰቦ ችና ህዝቦች ቋንቋዎች ሃይማኖቶችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እኩልነት መከበር አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣በደረጃቸው እነዚህን እኩልነቶች የሚፃረሩ ሁኔታዎችን ይዘረዝራሉ፣ሴቶች በትዳራቸውና በቤተሰብ ኑሮ ውስጥ ያላቸውን የእኩልነት መብት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣በቤተሰባቸውና በአካባቢያቸው የሴቶችን የእኩልነት መብቶችን ይለያሉ፣የአካል ጉዳተኞች መብቶች አለመከበራቸው ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳቶችን ይዘረዝራሉ፣የሃይማኖት ዕኩልነት መከበር ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ።

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የፌዴራል ሕገ መንግሥትን ምንነትና አስፈላጊነት ያብራራሉ፣እንደ ሕብረተሰብ አባልነታቸው ከነሱ የሚጠበቅ ሥነምግባርን ይገልፃሉ፣ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን መልካም ሥነምግባሮች ይላበሳሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የሥልጣን ገደብ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የቤተሰብ ሚስጥር ምንነት ይገልፃሉ፣የቤተሰብን ሚስጥር አለመጠበቅ የሚያስከትለውን ጉዳት ያብራራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 4. ፍትሐዊነት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 12**

- በዜጐች መካከል ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር ሊኖር እንደሚገባ ያውቃሉ።
- የፍትሕ አካላትን፣ የፍርድ አሰጣጥ ሂደትን ለይተው ይገነዘባሉ።
- የአገልግሎት ተቋማት ፍትሐዊ ሥርጭት ምንነትን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ከአድሎ የፀዳ አሠራር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br>• እነዚህ አሠራሮች ለሰላምና ለልማት ዕድገት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ያብራራሉ፣ | 4.1 ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ የሆነ አሠራር መኖር፣<br>(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- ለዴሞክራሲ ግንባታ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ፣<br>- ለዘላቂ ሰላም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ፣<br>- ለፈጣን ልማት መረጋገጥ የሚያበረክ ተው አስተዋጽኦ፣ | • ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር መኖር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች በየተራ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ማድረግ።<br>• ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር በሚለው ሀሳብ ላይ ግልጽነት ከተጨበጠ በኋላ ተማሪዎቹን በሦስት ቡድን በመክፈል አንዱ ቡድን ከአዱሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር ለዴሞክራሲ ግንባታ፣ ሌላኛው ለዘላቂ የሚኖረውን አስተዋጽኦ ተወያይተው ለክፍሉ እንዲያቀርቡና በጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • አድሎአዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣ | 4.2 አድሎአዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች፣<br>(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- ተነሳሽነት ማጣት፣<br>-ተስፋ መቁረጥ፣<br>-የምንቸገረኘነት ስሜት መደርጀት፣ | • ባለፈው ትምህርት ከአድሎ የፀዳና ፍትሐዊ አሠራር መኖሩ ለምን እንደሚጠቅም ተማሪዎቹ እንዲረዱ ተደርጓል። አሁን ደግሞ እነዚያው ቡድኖች አዱሎአዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸው ችግሮች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲወያዩና ለክፍ በማቅረብ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | -ለአመፅ መነሳሳት፣<br>-የሰላምና መረጋጋት መደፍረስ፣ | • በተቻለ መጠን ውይይቱ ወደ ተዘረዘሩት ይዘቶች እንዲያተኩር ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። |
| • የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ፍትሐዊ ሥርጭት ምንነት ይገልፃሉ፡ | 4.3 የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>4.3.1 የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፍትሐዊ ሥርጭት ፣ | • የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምንነት፣ የሚያሳዩት የአሰራር ብቃትና ፍትሐዊነትን በተመለከተ በቀደመው የክፍል ደረጃ ተምረው መጥተዋል። እዚህ ጋ ማሳየት የሚፈለገው የስርጭት ምንነትን ነው። በሀገሪቱ በነበረው ብልሹ አስተዳደር የተነሳ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሁሉም ክልሎች በፍትሐዊነት የተሰራጩ አልነበረም። ብዙዎቹ ይገኙ የነበሩት በአዲስ አበባና በሌሎች ዋና ዋና ከተሞች ብቻ ነበር። ለምሳሌ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በብዙ ክልሎች ይገኙ የነበሩት በአውራጃ ዋና ከተሞች ብቻ ነበሩ። በሌሎችም ዘርፎች ሁኔታው ይኸው ነበር። ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል በክልላቸው (በዞን ወይም በወረዳ) የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሥርጭታቸው ምን ያህል ፍትሐዊነት እንዳለው የወረዳ አስተዳደርን ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ማንኛውንም አካላትን በመጠየቅ ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላትን ይዘረዝራሉ፣<br>• በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላት አሰራር ፍትሐዊ መሆኑ የሚኖረውን ጠቀሜታ ያብራራሉ፣ | 4.4 በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>4.4.1 በአካባቢየሚገኙ የፍትህ አካላት ፍትሐዊ አሰራር አስፈላጊነት፣<br>- ትክክለኛና ከወገናዊነት የፀዳ ዳኝነት ለመስጠት፣<br>- ትክክለኛና ከወገናዊነት የፀዳ ዳኝነት መኖር፣ | • የፍትህ አካላት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ተማሪዎቹ በክለሳ መልክ እንዲዘረዝሯቸው ማድረግ። ትምህርቱን የበለጠ ተጨባጭ ለማድረግ እንዲያስችልም ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኝ ፍርድ ቤትን የፍርድ አሰጣጥ ሒደት እንዲመለከቱና ይህን ምልከታቸውን ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡ ማድረግ። ውይይቱ በዋንኛነት የፍርድ አሰጣጡ ምን ያህል ፍትሐዊ እንደሆነ፣ ትክክለኛ (ወገናዊ ያልሆነ) የፍርድ አሰጣጥ ሒደት የሚኖረው ጠቀሜታና ጠቀሜታውም ምን እንደሆነ የሚያመላክት መሆን ይኖርበታል። |

7ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | - ለዘላቂ ሰላም መስፈንና ለፈጣን ልማት መረጋገጥ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ፣ | |
| • መብቶቻቸው ሲጣሱ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራሉ፣<br>• መብቶቻቸው ሲጣሱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች በማሳወቅ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ፣<br>• ዜጎች ትክክለኛ ዳኝነት የማግኘት መብት እንዳላቸው ይገልፃሉ፣ | 4.5 መብቶች ሲጣሱና ፍትህ ሲጓደል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>4.5.1 መብቶችን የማስከበርና ፍትሕን የማስፈን እርምጃዎች፣<br>- ክስ፣<br>-ይግባኝ፣ | • መብቶች በተለያዩ ምክንያቶች ሊጣሱ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህልም ከተሰጠ ሥልጣን ውጪ በመሥራት የዜጎች መብቶች ሊጣሱ ይችላሉ። መብቶች ሲጣሱ በዝምታ ከመመልከት ይልቅ መብትን ማስከበር አስፈላጊ ነው። የተጣሰን መብት ለማስከበርም ደግሞ ሁልጊዜ ሕጋዊ መንገድን መጠቀም ተገቢ ነው። ስለሆነም ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል መብቶቻቸው ሲጣሱ እንዴት ማስከበር እንደሚገባቸው እንዲወያዩና ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የግብር ከፋዮችን ግዴታና መብቶች ይዘረዝራሉ፣<br>• ሁሉም ግብር ከፋይ ግብሩን እንዲከፍል ከሕብረተሰቡ የሚጠበቁ ኃላፊነቶችን ይገልፃሉ፣ | 4.6 ግብር፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>4.6.1 የግብር ከፋዮች መብት፣ግዴታዎችና የሕብረተሰብ ኃላፊነት<br>-የግብር ከፋዮች ግዴታዎች<br>-የግብር ከፋዮች መብቶች፣<br>-ከሕብረሰብ የሚጠበቅ ግዴታ፣ | • ግብር መሠረታዊ የሆነ የመንግሥት ገቢ ነው። ግብርን በመሰብሰብ መንግሥት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ቀደም ባለው ክፍል እንዲያውቁት ተደርጓል። ግብር በመሰብሰብ መንግሥት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ተማሪዎች በክለሳ መልክ እንዲያብራሩ ማድረግ።<br>• ግብር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው መግባባት ላይ ከተደረሰ በኋላ በየደረጃው ከግብር ከፋዮችና ከሕብረተሰቡ ምን እንደሚጠበቅ ተማሪዎች እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ከአድሎ የፀዳ አሠራር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይዘረዝራሉ፣እነዚህ አሠራሮች ለሰላምና ለልማት ዕድገት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፣አድሎአዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ፍትሐዊ ሥርጭት ምንነት ያውቃሉ፡በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላትን ይዘረዝራሉ፣በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላት አሰራር ፍትሐዊ መሆኑ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይለያሉ፣መብቶቻቸው ሲጣሱ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራሉ፣መብቶቻቸው ሲጣሱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች  ያሳውቃሉ፣ዜጐች ትክክለኛ ዳኝነት የማግኘት መብት እንዳላቸው ያውቃሉ፣የግብር ከፋዮችን ግዴታና መብቶች ይዘረዝራሉ፣ሁሉም ግብር ከፋይ ግብሩን እንዲከፍል ከሕብረተሰቡ የሚጠበቁ ኃላፊነቶችንይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የከአድሎ የፀዳ አሠራር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይዘረዝራሉ፣እነዚህ አሠራሮች ለሰላምና ለልማት ዕድገት የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፣አድሎአዊ አሠራሮች የሚያስከትሏቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ፍትሐዊ ሥርጭት ምንነት ያውቃሉ፡በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላትን ይዘረዝራሉ፣በየደረጃው የሚገኙ የፍትህ አካላት አሰራር ፍትሐዊ መሆኑ የሚኖረውን ጠቀሜታ ይለያሉ፣መብቶቻቸው ሲጣሱ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ይዘረዝራሉ፣መብቶቻቸው ሲጣሱ ለሚመለከታቸው ክፍሎች  ያሳውቃሉ፣ዜጐች ትክክለኛ ዳኝነት የማግኘት መብት እንዳላቸው ያውቃሉ፣የግብር ከፋዮችን ግዴታና መብቶች ይዘረዝራሉ፣ሁሉም ግብር ከፋይ ግብሩን እንዲከፍል ከሕብረተሰቡ የሚጠበቁ ኃላፊነቶችንይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 5. የሀገር ፍቅር

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 9**

- የህዝብና የሀገርን ትክክለኛ ታሪኮችንና ባህሎችን ጠንቅቆ በመገንዘብ አዲሱን የሀገር ፍቅር ስሜት ያዳብራሉ፣
- የጋራ ደህንነት ሊያናጉ የሚችሉ አፍራሽ ጐጂ ልማዶችን ይዋጋሉ፣

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣<br>• የሀገርና የሕዝብ ትክክለኛ ታሪክ ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣<br><br>• በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው አንዳቸው ለሌላው መልካም ምሳሌ የሚሆን ተግባር ያከናውናሉ፣ | 5.1 የሀገር ፍቅር፣ (3 **ክፍለ ጊዜ**)<br>5.1.1 የአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎች፣<br>- ለሕግና ደንብ ተገዥ መሆን፣<br>- የሌሎች ሰዎችን መብቶች ማክበር፣<br>- የተሰጠን ኃላፊነትን በብቃት መወጣት፣<br>- ለሕብረተሰብ አርአያነት ያላቸውን ተግባራት መፈጸም፣<br>- የሀገርና የህዝብ ትክክለኛ ታሪኮችንና ባህሎችን መገንዘብ፣<br>- በሀገራችን የተዛቡና ያልተዛቡ ታሪኮችን የማስተካከል አስፈላጊነት፣ | • ሀገሬን እወዳለው ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ስለሆነም ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል ያላቸውን የሀገር ፍቅር እንዴት እንደሚገልጹ ተወያይተው ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ማድረግ። በሌላ በኩል ለሀገር ፍቅር መኖር የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ታሪክ ያለአድሎዎ በትክክል ሊፃፍ ይገባዋል። ይህ ትምህርት ተማሪዎቹ እንዳይከብዳቸው ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ ትክክለኛ ታሪክ የሚባለው በማስረጃ ላይ የተመሠረተና አድሎአዊ ያልሆነ ታሪክ ማለት እንደሆነ ተማሪዎቹ እንዲረዱ በማድረግ አወያይቶ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • በአካባቢያቸው የሚታዩ ልዩ ልዩ አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን ይከላከላሉ፣ | 5.2 አፍራሽና ጐጂ ተግባራት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**) | • በአካባቢያችን በርካታ አፍራሽና ጐጂ ተግባራት ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ምንም ዓይነት ሥራ ሳይሰሩ ቁጭ ብሎ መዋል። ተማሪዎቹን በቡድን |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የትምህርት ቤታቸውንና በአካባቢያቸው የሚገኙ መገልገያ ንብረቶችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣ | 5.2.1 በአካባቢያችን የሚታዩ አፍራሽና ጐጂ ተግባራት<br>- የጋራ መገልገያ ንብረቶችን በጥንቃቄ አለመያዝ የሚያስከትለው ጉዳት፣ | በመክፈል በአካባቢያቸው በሚመለከቷቸው አፍራሽና ጐጂ ተግባራት ላይ ተወያይተው ከነመፍትሔያቸው እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። ውይይታቸው ለምሳሌ በመኖሪያ አካባቢ የሚታዩ አፍራሽ ተግባራት እንዴት የህዝብን ሰላምና የጋራ ደህንነት ሊያናጉ እንደሚችሉ ተጨባጭ ማስረጃዎችን ማቅረብ። ከዚህም ባሻገር ውይይታቸው በአካባቢያቸው ያሉት የጋራ መገልገያ ንብረቶችን (ለምሳሌ የውሀ መውረጃ ቦይን፣ የጋራ መጸዳጃ ቤትን ወዘተ) በጥንቃቄ አለመያዝ የሚያስከትለውን ጉዳት ትኩረት ሊያደርግበት ይገባዋል። |
| • የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድህነትን በመዋጋት በኩል ያላቸውን ቦታ ያብራራሉ፣ | 5.3 የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>5.3.1 ለሀገራችን ልማት የወጡ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድህነትን በመዋጋት በኩል ያላቸው ሚና፣<br>5.3.2 የጋራ ችግርችን ለማስወገድ የበጐ ፈቃደኝነት ሚና፣ | • ኢትዮጵያ ድህነትን በማስወገድ ረገድ የተለያዩ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ቀረጻ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጋለች። በዚህም ጥሩ ወጤት ተመዝግቧል። ለምሳሌ የኢኮኖሚው ፖሊሲ ስትራቴጂ ከሆነው ውስጥ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ዕድገት ነው። እንዲህ እያሉ ተማሪዎቹ ሌሎቹንም እንዲያውቋቸው በማድረግ እንዲወያዩባቸው ማድረግና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የዜጐችን መብትና ግዴታዎች ያብራራሉ፣<br>• በደረጃቸው ያሉዋቸውን መብቶችና ግዴታዎች ይዘረዝራሉ፣ | 5.4 ዜግነት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>5.4.1 የዜጐች መብትና ግዴታ፣ | • ትምህርቱን እንደ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎቹ አለን የሚሉዋቸውን መብቶችና ግዴታዎች እንዲገልጹ በማድረግ መጀመር።<br>• በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል የክልልና የፌዴራል ሕገመንግሥቶችን በመመልከት መብትና ግዴታቸውን ዘርዝረው ለክፍል ውይይት እንዲያቀርቡና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ታሪካዊ ሒደት ያብራራሉ፣ | 5.5 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፣ **(1ክፍለ ጊዜ)**<br>5.5.1 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በታሪክ ያለፈባቸው | ተማሪዎች ስለ ሰንደቅ ዓላማ አስፈላጊነት በራሳቸው በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ።<br>• ከዚህም ላይ ተነስቶ ስለ ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በታሪክ ያለፈባቸውን ሒደቶች ማብራሪያ መስጠት። አሁን ስላለው የኢትዮጵያ ሰንደቅ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | ሂደቶች፣ | ዓላማና ለሰዓርማው ትርጉም ተማሪዎቹ የራሣቸውን ማብራሪያ እንዲሰጡ በማድረግ ለትምህርቱ ማጠናከሪያ በመስጠት ማጠናቀቅ፣ |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ከአዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣የሀገርና የሕዝብ ትክክለኛ ታሪክ ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው አንዳቸው ለሌላው መልካም ምሳሌ የሚሆን ተግባር ያከናውናሉ፣በአካባቢያቸው የሚታዩ ልዩ ልዩ አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን ይዘረዝራሉ፣የትምህርት ቤታቸውንና በአካባቢያቸው የሚገኙ መገልገያ ንብረቶችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድህነትን በመዋጋት በኩል ያላቸውን ቦታ ይዘረዝራሉ፣የዜጐችን መብትና ግዴታዎች ይዘረዝራሉ፣በደረጃቸው ያሉዋቸውን መብቶችና ግዴታዎች ይዘረዝራሉ፣የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ታሪካዊ ሒደት ይለያሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፣የሀገርና የሕዝብ ትክክለኛ ታሪክ ምን ማለት እንደሆነ ይገልፃሉ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው አንዳቸው ለሌላው መልካም ምሳሌ የሚሆን ተግባር ያከናውናሉ፣በአካባቢያቸው የሚታዩ ልዩ ልዩ አፍራሽና ጐጂ ተግባራትን ይከላከላሉ፣የትምህርት ቤታቸውንና በአካባቢያቸው የሚገኙ መገልገያ ንብረቶችን በጥንቃቄ ይይዛሉ፣የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ድህነትን በመዋጋት በኩል ያላቸውን ቦታ ያብራራሉ፣የዜጐችን መብትና ግዴታዎች ያብራራሉ፣በደረጃቸው ያሉዋቸውን መብቶችና ግዴታዎች ይዘረዝራሉ፣የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ታሪካዊ ሒደት ያብራራሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

**6. የኃላፊነት ስሜት**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍል ጊዜ** 10

- የተለያዩ የኃላፊነት ዓይነቶችንና ደረጃዎችን ያውቃሉ።
- የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን የመንከባከብ ኃላፊነትን ይረዳሉ።
- እራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዴት እንደሚጠብቁ ይገነዘባሉ፣

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የኃላፊነት ዓይነቶችና ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው የሚገቡትን ቃል ኪዳን ያከብራሉ፣ | 6.1 ኃላፊነት መወጣት፣ (**2 ክፍለ ጊዜ**)<br>6.1.1 የኃላፊነት ዓይነቶችና ደረጃዎች | • ኃላፊነት ባጠቃላይ ብቻ የሚታይ ጉዳይ ሳይሆን ዓይነቶችና ደረጃዎች አሉት። ለምሳሌ ከተማሪ የሚጠበቅ ኃላፊነት አለ፣ ከመምህር የሚጠበቅ ኃላፊነት አለ፣ ከርዕሰ መምህር የሚጠበቅ ኃላፊነት አለ። ከጠቅላይ ሚኒስትር የሚጠበቅ ኃላፊነት አለ ወዘተ. ከዚህም ባሻገር የኃላፊነት ደረጃዎች አሉ፣ ለምሳሌ ሁሉም ተማሪ የተማሪነት ኃላፊነት ቢኖርበትም የክፍል አለቃ የተለየ ኃላፊነት አለበት።<br>• እንደዚሁም ዜጎች ሁሉ ሀገራቸውን በተመለከተ ኃላፊነት ቢኖርባቸውም ከያዘው ሥልጣን በመነጨ ጠቅላይ ሚኒስትር የተለየ ኃላፊነት አለበት። በዚህ መሠረት የተለያዩ ርዕሶችን ለተማሪዎች በቡድን በመስጠት እንዲወያዩበትና ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ። |
| • ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ፣ለተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ብክነት መንስዔ የሆኑትን ጉዳዮች ይዘረዝራሉ፣ | 6.2 ቃል ኪዳን፣ (**2 ክፍለ ጊዜ**)<br>-በትምህርት ቤትና በአካባቢያችን ቃልኪዳናችንን ማክበር፣<br>-በአካባቢያችን የሚሰጠንን ኃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝ ነትና በሐቀኝነት መወጣት፣ | • ተማሪዎች በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው ሊገቡ የሚችሏቸው ቃል ኪዳኖች (ለምሳሌ የክፍልንና የትምህርት ቤታቸውን ጽዳት መጠበቅና ማስዋብ ሊሆን ይችላል) ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ በቡድን ተከፋፍለው እንዲለዩና እነዚህን ቃል ኪዳኖች ለማብከርም ከነሱ ምን እንደሚጠበቅ እንዲወያዩ ማድረግ። ይህን ውይይት የበለጠ በክፍል ውይይት በማጠናከር ተማሪዎች የራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | • በሌላ በኩል ምንም ዓይነት ኃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሐቀኝነት መወጣት አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም። በዚህም ጉዳይ ላይ ተማሪዎቹ እንዲወያዩና የጋራ አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ። |
| • የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣ | 6.3 የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>-የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ብክነት መንስዔዎች፣<br>-የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶች የመጠበቅና የማልማት ኃላፊነት፣ | • ለክለሳ በሚያገለግል መልኩ የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ምን እንደሆኑና ባካባቢያቸው የሚገኙትን እንዲዘረዝሩ ማድረግ። እነዚህ ሀብቶች ከታሪካዊና ማህበራዊ ፋይዳቸው ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እንዴት እንደሚገለጽ እያንዳንዱ ተማሪ እንዲያስረዳ ማድረግ።<br>• ከዚያም ተማሪዎቹን በቡድን በመከፋፈል ለነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ጉዳትና ብክነት መንስዔ የሚሆኑ ምክንያቶች ምን እንደሆኑና በነሱ ደረጃ ምን እንክብካቤ ሊያደርጉ እንደሚገባቸው በመወያየት የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ።<br>• አቅም በፈቀደ ታሪካዊ ሥፍራዎችንም እንዲበኙ ማድረግ። |
| • ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በህብረተሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ይዘረዝርሉ፣<br>• ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች እራሳቸውን ይጠብቃሉ፣ | 6.4 ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፡ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>-በህብረተሰብ ላይ እያደረስ ያለው ጉዳት፣<br>-ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን መከላከያ ዘዴው፣ | • እያንዳንዱ ተማሪ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ምን ያህል አስከፊ በሽታ እንደሆነ የራሱን አመለካከት እንዲሰጥ ማድረግ። አስከፊነቱን በተመለከተ የሚያውቁት የአካባቢ ማስረጃ ካለ እንዲያቀርቡ ማበረታታት። ለምሳሌ እናትና አባታቸው በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በመሞታቸው የተነሳ ያለ አሳዳጊ የቀሩ ሕፃናት በማስረጃነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በማስከተልም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ሕብረተሰቡ እንዴት መከላከል እንደሚገ ባው ተወያይተው ለክፍሉ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት፡፡ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃር መሆን ይኖርበታል ፡፡በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የኃላፊነት ዓይነቶችና ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው የሚገቡትን ቃል ኪዳን ይዘረዝራሉ፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ፣ለተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ብክነት መንስዔ የሆኑትን ጉዳዮች ይዘረዝራሉ፣የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በህብረተሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ይዘረዝርሉ፣ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች እራሳቸውን ይጠብቃሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የኃላፊነት ዓይነቶችና ደረጃዎችን ይዘረዝራሉ፣በትምህርት ቤትና በአካባቢያቸው የሚገቡትን ቃል ኪዳን ያከብራሉ፣ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ይወጣሉ፣ለተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ብክነት መንስዔ የሆኑትን ጉዳዮች ይዘረዝራሉ፣የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ይንከባከባሉ፣ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በህብረተሰብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጉዳት ይዘረዝርሉ፣ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ከሚተላለፍባቸው መንገዶች እራሳቸውን ይጠብቃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል፡፡

**7. ጠንካራ የሥራ ባህል**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 7**

- ማንኛውንም የሥራ መስክ መናቅ እንደሌለበት ይገነዘባሉ።
- የሥራንና የጊዜን ክቡርነት ይረዳሉ።
- የሙያ ችሎታን ማዳበር ለምርታማነትና ለዕድገት መሠረት መሆኑን ይረዳሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የሥራን ክቡርነት በተግባር ያሳያሉ፣<br>• የጊዜ፣ የሥራና የልማት ግንኙነትን ያብራራሉ፣<br>• የሚሰሯቸውን ሥራዎች በወቅቱና በጥራት ያከናውናሉ፣ | 7.1 የሥራ ባህልን ማዳበር፣<br>**(3 ክፍለ ጊዜ)**<br>7.1.1 አንድ የሥራ መስክ ከሌላው የማያንስ መሆኑን፣<br>-የጊዜ፣ የሥራና የልማት ግንኙነት፣<br>-የግልና የጋራ ሥራዎችን በሁሉም ሥፍራ በወቅቱና በጥራት ማከናወን፣ | • የተለያዩ የሥራ መስኮችን በምሳሌነት በማቅረብ ተማሪዎች የትኛው የሥራ መስክ እንደሚበልጥ በቡድን እንዲከራከሩ ማድረግ። ክርክሩ ምንም መልክ ቢኖረው ዞሮ ዞሮ ድምዳሜው ማንኛውም የሥራ መስክ ክቡር እንደሆነና ለግልም ሆነ ለሀገር ዕድገት ጠቃሚ እንደሆነ የሚያስገነዝብ መሆን አለበት።<br>• በሌላ በኩል ተማሪዎች ተወያይተው የራሳቸውን ድምዳሜ መስጠት ያለባቸው ጉዳይ ሥራ ሊከናወን የሚገባው በጊዜ ውስጥ ነው። አንድ ሥራ በተያዘለት ጊዜና በሚጠበቀው ጥራት ካልተሠራ ተሠራ ለማለት አይቻልም። ስለሆነም ሥራን በጊዜውና በሚፈለገው ጥራት ማከናወን ልማትን ማፋጠን ነው። ይህን ጉዳይ ተማሪዎች እንዲወያዩበትና በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • ሳይሰሩ መኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች ያብራራሉ፣ | 7.2 ሳይሰሩ መኖር፣(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>7.2.1 ሳይሰሩ መኖር የኢኮኖሚ፣ የልማትና የዕድገት ፀር ነው፣ | • ሳይሰሩ መኖርን በተመለከተ ተማሪዎች ምን እንደሚረዱ እንዲገልፁ ማድረግ። ለምሳሌ በነሱ ደረጃ ሳይሰሩ መኖር ትምህርታቸውን ባለመማር፣ ወይም ገቢ ሊያስገኝ የሚችል ሥራ ባለመስራትና ነገር ግን ቤተሰብ ሠርቶ ባገኘው ገቢ ላይ ተንጠልጥሎ በመኖር ሊገለጥ ይችላል። ይህ እጅግ አስነዋሪ |
| • በሕገመንግሥቱ የተደነገገ ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፣ | 7.2.2 ኢፌድሪ ሕገመንግሥት የተደነገጉ ኢኮኖሚ መብቶች | • ተግባር ሲሆን ድምር ውጤቱም የሀገርን ልማትና ዕድገትየሚያዳክም ነው የሚሆነው። ስለሆነም ሳይሰሩ መኖር ለግለሰቡም ሆነ ለሀገር ያለውን ጉዳት በተመለከተ እንዲወያዩና የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ፣ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| | | የፌዴራል ሕገመንግሥትን በማጣቀስም የተደነገጉ የኢኮኖሚ ዓላማዎችን ተማሪዎች እንዲረዱቸው ማድረግ። |
| • የሙያ ችሎታና ሥነምግባርን ማሳደግ ከምርታማነት ጋር ያላቸውን ትስስር ይገልፃሉ፣ | 7.3 የሙያ ችሎታና ሥነምግባር፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>7.3.1 የሙያ ችሎታና ሥነምግባርን ማሳደግ ምርታማነትን ከማሳደግ ጋር ያላቸው ግንኙነት፣ | • ሙያ አንድን ሥራ ለማከናወን በተፈጥሮ ወይም በሥልጠና የሚገኝ ችሎታ እንደሆነ ተማሪዎች እንዲገነዘቡት ማድረግ። የሙያ ሥነምግባር ደግሞ ሙያው ከሙያተኛው የሚፈለገው ባህሪና ዝንባሌ መሆኑን እንዲያውቁት ማድረግ። በዚህ ረገድ ከመምህራን የሚጠበቅ የሙያ ሥነምግባር አለ፣ ከህክምና አዋቂዎች የሚጠበቅ የሙያ ሥነምግባር አለ ወዘተ፣ እነዚህ ሁለት ነገሮች (ሙያና የሙያ ሥነምግባር ) ካልተሟሉ በምንም ዓይነት ሥራ ውጤታማ መሆን አይችልም።<br>• ስለሆነም ለተማሪዎች ተጨማሪ ምሳሌዎችን በመስጠት የሙያ ችሎታና ሥነምግባር ከምርታማነት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ እንዲረዱና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማወያየት። |

# ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የሥራን ክቡርነት በተግባር ያሳያሉ፣የጊዜ፣ የሥራና የልማት ግንኙነትን ይዘረዝራሉ፣የሚሰሯቸውን ሥራዎች በወቅቱና በጥራት የማከናወን ጠቀሜታን ይዘረዝራሉ፣ሳይሰሩ መኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች ይዘረዝራሉ፣በሕገመንግሥቱ የተደነገጉ ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፣የሙያ ችሎታና ሥነምግባርን ማሳደግ ከምርታማነት ጋር ያላቸውን ትስስር ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የሥራን ክቡርነት በተግባር ያሳያሉ፣የጊዜ፣ የሥራና የልማት ግንኙነትን ያብራራሉ፣የሚሰሯቸውን ሥራዎች በወቅቱና በጥራት ያከናውናሉ፣ሳይሰሩ መኖር የሚያስከትላቸውን ችግሮች ያብራራሉ፣በሕገመንግሥቱ የተደነገጉ ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች ምን እንደሆኑ ይዘረዝራሉ፣የሙያ ችሎታና ሥነምግባርን ማሳደግ ከምርታማነት ጋር ያላቸውን ትስስር ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ** የሆኑ ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 8. ራስን መቻል

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 7**

- የጥገኝነት አስከፊነትን ይገነዘባሉ።
- የራስን ችሎታ ማወቅ፣
- ለላቀ ሥራ ውጤት ክብር መስጠትና ከሌሎች መማር በራስ ለመተማመንን ያለውን ጠቀሜታ ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የጥገኝነትን አስከፊ ገጽታ ይገልፃሉ፣<br>• ከጥገኝነት እራሳቸውን ለማላቀቅ ጥረት ያደርጋሉ፣ | 8.1 ራስን የመቻል ባህልን ማዳበር፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>8.1.1 ጥገኝነትን ማስወገድ፣<br>- ጥገኝነት ራስን ለመም ራት ራስን ለመቻልና በራስ የመተማመንን ባህሪ እንዳይዳብር በማድረግ ረገድ ያለው አስተዋፅኦ፣<br>8.1.2 ጥገኝነትና የኮንትሮባንድ ንግድ፣<br>- ኮንትሮባንድ ንግድ ለመከላከል የወጡ ሕጐችና ያስገኘው ውጤት፣ | • ለክለሳም እንዲያገለግል «ራስን መቻል» የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ ተማሪዎች በየተራ እንዲገልጹና ከጥገኝነት በምን እንደሚለይ እንዲያብራሩ ማድረግ። በማስከተልም የጥገኝነት መገለጫ ባህሪዎች ምን እንደሆኑ እንዲያስረዱ ማበረታታት። ለምሳሌ በነሱ ደረጃ ጥገኝነት ትምህርታቸውን ማንኛውንም ችግር ተቋቁመው ከመማር ይልቅ የተለያዩ ነገሮች አልተሟሉልንም በማለት ትምህርታቸውን ማቋረጥና ምንም ሥራ ሳይሰሩ በቤተሰብ ትከሻ ላይ በመኖር ይገለጣል። ይህ ዝንባሌ ደግሞ ወደፊት ተምሬ እንዲህ እሆናለሁ የሚለውን ተስፋ አጨልሞ ራስን ለመቻል የሚኖር ዓላማንና በራስ የመተማመን ስሜትን ይገድላል።<br>• በነዚህና በሌሎችም ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች እንዲወያዩና የራሳቸውን ዳምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • ለላቀ የሥራ ውጤት ክቡር መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ያብራራሉ፣<br>• ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት | 8.2 ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት፣ **(2 ክፍለ ጊዜ)**<br>-ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት ማለት ምን ማለት | • ከሁሉ በፊት ተማሪዎቹ በየተራ ለጥሩ ሥራ እውቀና(ክብር) ይሰጡ እንደሆነ እንዲገልጹ ማድረግ። ለምሳሌ በራሱ ተግቶ እየሰራ ጉበዝ ለሆነ የክፍላቸው ተማሪ ተገቢውን ክብር መስጠት ተገቢ ነው። ጥሩ ሥራ የሥራ ሰው አድናቆት ሲቸረው የበለጠ |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣<br>• የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋሉ፣ | ነው?<br>-ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት በምን ይገለፃል? | ለመሥራት ይነሳሳል። ብዙ ጊዜ ሰዎች የሰሩትን ማናናቅ እንጂ ማድነቅ አይስተዋልም። ይህ ከፍተኛ ስሕተትና ኋላቀር ልማድ ነው፣ የተለያዩ ሳይንቲስቶችን፣ ፀሐፊዎችን፣ ፈላስፎችን፣ አሳሾችን፣ መሪዎችን፣ አስተማሪዎችን ወዘተ ታላላቅ ሥራዎችን በምሳሌነት ተጠቅሞ የላቀ የሥራ ውጤት ማለት ምን እንደሆነ ተማሪዎቹ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ማድረግ። የነዚህ ሰዎች የሥራ ውጤቶች የምንኖርባት ዓለምን በመለወጥ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፣ ለሰዎቹ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት ያስፈልጋል። ክብር ለመስጠት ግን ሥራዎቹ ያመጡትን ለውጥ በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል።<br>• ተማሪዎቹ በቀረበላቸው የታላላቅ ሰዎች ሥራዎች ላይ እንዲወያዩና ክብር እንዴት እንደሚሰጡ እንዲያስረዱ በማድረግ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲያቀርቡ ማስቻል። |
| • በራስ መተማመን ለላቀ የሥራ ውጤት ለመብቃት ያለውን ከፍተኛ ድርሻ ያብራራሉ፣<br>• የሌሎችን አስተሳሰብና አመለካከት ሳይንቁ የራስን አስተሳሰብና አመለካከት ማራመድ ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ፣ | 8.3 በራስ መተማመን፣ (**2 ክፍለ ጊዜ**)<br>8.3.1 በራስ መተማመን ለላቀ የሥራ ውጤት ለመብቃት ያለው ወሳኝ ሚና፣<br>8.3.2 የሌሎችን አስተሳሰብና አመለካከት በግልጽነትና በአግባቡ በማስተናገድ የራስን አመለካከትና እምነት በጽናት ማራመድ፣ | • «በራስ መተማመን» የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ምን ማለት እንደሆነ ተማሪዎች በክለሳ መልክ እንዲወያዩበት ማድረግ። እነሱ በራስ መተማመን ስሜት እንዳላቸውና ይህም እንዴት እንደሚገለጽ እንዲያስረዱ ማድረግ። ለምሳሌ በነሱ ደረጃ በራስ የመተማመን ስሜት በርግጠኝነት ትምህርቴን ጨርሼ ሳይንቲስት እሆናለሁ በሚል ሊገጽ ይችላል። ስለሆነም በአንድ ሰው ውጤታማነት ላይ በራስ መተማመን ከፍተኛ ድርሻ አለው። በዚህም መሠረት ለተማሪዎቹ የተለያዩ ጉዳዮችን (Case Studies) በማቅረብ በራስ መተማመን በውጤታማነት ላይ ያለውን ተፅዕኖ እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ።<br>በሌላ በኩል በራሱ የሚተማመን ሰው የሌሎችን ሀሳብ ለማዳመጥ፤ ትክክልም ሆኖ ከተገኘ ሀሳባቸውን ለማስተናገድ አይቸገርም፣ ሀሳባቸውም ትክክል ካልሆነ ትክክል አለመሆናቸውን በማስረዳት የራሱን ትክክለኛ ሀሳብ በጥንካሬ ያራምዳል። ተማሪዎቹ በነዚህም ጉዳዮች ላይ እንዲወያዩና የጋራ አመለካከት እንዲይዙ ማስቻል። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ  ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና  በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የጥገኝነትን አስከፊ ገጽታይዘረዝራሉ፣ከጥገኝነት እራሳቸውን ለማላቀቅ ጥረት የማድረግ ጠቀሜታን ይዘረዝራሉ፣ለላቀ የሥራ ውጤት ክቡር መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይገልጻሉ፣ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት አስፈላጊነትን ይዘረዝራሉ፣የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋሉ፣በራስ መተማመን ለላቀ የሥራ ውጤት ለመብቃት ያለውን ከፍተኛ ድርሻ ይዘረዝራሉ፣የሌሎችን አስተሳሰብና አመለካከት ሳይንቁ የራስን አስተሳሰብና አመለካከት ማራመድ ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የጥገኝነትን አስከፊ ገጽታ ይገልፃሉ፣ከጥገኝነት እራሳቸውን ለማላቀቅ ጥረት ያደርጋሉ፣ለላቀ የሥራ ውጤት ክቡር መስጠት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ያብራራሉ፣ለላቀ የሥራ ውጤት ክብር መስጠት አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋሉ፣በራስ መተማመን ለላቀ የሥራ ውጤት ለመብቃት ያለውን ከፍተኛ ድርሻ ያብራራሉ፣የሌሎችን አስተሳሰብና አመለካከት ሳይንቁ የራስን አስተሳሰብና አመለካከት ማራመድ ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ  የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

9. **ቁጠባ ባህል**

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 6**

- የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎች መኖራቸውን ያውቃሉ።
- ማንኛውም ሰው ራሱንና ቤተሰቡን በአቅሙ ልክ ማስተዳደር እንዳለበት ይረዳሉ።
- በዕቅድ በመመራት የቁጠባን ባህል ማዳበር እንደሚያስፈልግ ይገነዘባሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • የቁጠባ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣<br>• የጥናት ጊዜን በአግባቡ ይጠቀማሉ፣ | 9.1 የቁጠባ ዓይነቶች፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>9.1.1 በዓይነት የሚደረግ ቁጠባ፣<br>9.1.2 በገንዘብ የሚደረግ ቁጠባ፣<br>9.1.3 የጊዜ የሚደረግ ቁጠባ፣ | • ለክለሳ በሚረዳ መልኩ ተማሪዎች የቁጠባን አስፈላጊነት በተመለከተ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩ ማድረግ። በቁጠባ አስፈላጊነት ላይ መግባባት ከተደረሰ በኋላ በቡድናቸው ውስጥ የቁጠባ ዓይነቶች ሊሆኑ ይችላሉ የሚሏቸውን እንዲዘረዝሩና እንዲወያዩባቸው ማድረግ። ለምሳሌ አሁንም በሕብረተሰባችን በቂ ግንዛቤ ያላገኘው ጉዳይ በጊዜ ላይ የሚደረግ ቁጣበን ነው። በርግጥ የጊዜ ቁጠባ እንደሌሎች ነገሮች በጆንያ ወይም በካዝና የሚቀመጥ ሳይሆን በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙና ውጤታማ ሥራዎችን በመሥራት የሚገለጽ ነው። ስለዚህ ተማሪዎቹ በእንደዚህ ዓይነት እየተወያዩ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ መምህሩ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሃሳብ በመስጠት እንዲወያዩ ማድረግ። |
| • የቁጠባ ባህል አለመዳበር ድህነትን በማስፋት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ያስረዳሉ፣ | 9.2 የቁጠባ ባህል፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>- የቁጠባ ባህል አለመዳበር ድህነትን በማጠናከር ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ፣ | • ድህነትን ለመዋጋት ጠንክሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ የታወቀ ጉዳይ ነው፣ ነገር ግን ጠንክሮ በመሥራት የሚገኝ ገቢን ወይም ንብረትን ባግባቡና በቁጠባ መጠቀም ካልተቻለ ድህነትን ማስወገድ አይቻልም፣ ስለሆነም የቁጠባ ባህልን አለማዳበር ድህነትን ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት እንዴት እንደሚጐዳ ተማሪዎች በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ፣ |
| • በእቅድ አለመመራት የሚያስከትለውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣<br>• ሳምንታዊ ዕቅድ አዘጋጅተው | 9.3 በእቅድ መመራት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>9.3.1 በአቅም ልክ አለመመራት | • ተማሪዎች በእቅድ መመራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በክለሳ መልክ እንዲወያዩበትና እነሱን በተመለከተ እንዴት እንደሚገለጽ እንዲያስረዱ ማድረግ። ለምሳሌ እነሱን በተመለከተ የሳምንታዊ የጥናት ፕሮግራሞችን፣ በሳምንቱ ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራትን ቅደም |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይጠቀማሉ፣ | የሚያስከትላቸው ችግሮች፣<br>9.3.2 በእቅድ አለመመራት የሚያስከትላቸው ችግሮች፣ | ተከተል በማዘጋጀትና ተግባራዊ በማድረግ ሊገለፅ ይችላል፣። እንዲሁም ዕቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ጊዜን ባግባቡ ለመጠቀምና አንድን ተግባር በወቅቱ ለማከናወን ይረዳል፣። ይህን አለማድረግ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከትላል። ስለሆነም ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል በእቅድና በአቅም ልክ አለመመራት የሚያስከትላቸው ችግሮች ላይ ተወያይተው ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** የየቁጠባ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣የጥናት ጊዜን በአግባቡ ይጠቀማሉ፣የቁጠባ ባህል አለመዳበር ድህነትን በማስፋት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፣በእቅድ አለመመራት የሚያስከትለውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣ ሳምንታዊ ዕቅድ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** የቁጠባ ዓይነቶችን ይዘረዝራሉ፣የጥናት ጊዜን በአግባቡ ይጠቀማሉ፣የቁጠባ ባህል አለመዳበር ድህነትን በማስፋት ረገድ ያለውን አስተዋጽኦ ያስረዳሉ፣በእቅድ አለመመራት የሚያስከትለውን ጉዳት ይዘረዝራሉ፣ ሳምንታዊ ዕቅድ አዘጋጅተው ይጠቀማሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 10. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 4**

- በአካባቢ.ያዊና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ወሳኝ መሆኑን ይረዳሉ።
- የሲቪክ ማህበራት ሚናዎችን ይገነዘባሉ፣
- በሲቪክ ማህበራት መሳተፍ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • በአካባቢ የልማት ዘመቻ ላይ በንቃት ይሳተፋሉ፣ | 10.1 በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>10.1.1 በአካባቢ የልማት ዘመቻ ላይ በንቃት መሳተፍ፣<br>10.1.2 ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱን ማጠናከር፣<br>10.1.3 በኢትዮጵያ ውስጥ ፈጣን የልማት ዕድገት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በሕዝባዊ ተሳትፎ ማገዝ፣ | • ተማሪዎች በአካባቢያቸው ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን በየተራ እንዲገልፁ ማድረግ። ለምሳሌ በአካባቢያቸው ትኩረት የሚሻ ጉዳይ የአካባቢ ጽዳት ሊሆን ይችላል። ወይም የአካባቢ የልማት ጉዳይ ሊሆን ይችላል። በተማሪዎቹ የአካባቢ ጉዳዮች ከተለዩ በኋላ ለእነዚህ ጉዳዮች መፍትሔ መስጠት ያለበት ማን እንደሆነ፤ የነሱስ ሚና ምን መሆን እንደሚገባው ተማሪዎቹ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና ለክፍል እንዲያቀርቡ በማድረግ በራሳቸው ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማስቻል። ዋናው ግንዛቤ ማግኘት የሚገባው ጉዳይ ሁሉም ነገር ለመንግሥት የሚተው ሳይሆን ዜጎች በአካባቢና ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት መሳተፍ የሚገባቸው መሆኑን ተማሪዎች መረዳታቸው ነው። |
| • ለተሳትፎ የሚያገለግሉ ተቋሞችን ሁኔታ ይገልፃሉ፣<br>• የሲቪክ ማህበራት አደረጃጀትና ዓላማን ይገልፃሉ፣ | 10.2 የሲቪክ ክበባት/ ማህበራት ተግባራት፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>10.2.1 የሲቪክ ማህበራት መጠናከር ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ መጐልበት የሚኖረው ጠቀሜታ፣ | • ተማሪዎች ስለሲቪክ ማህበራት የሚያውቁትን እንዲገልጹ ማድረግ። ይህም የሲቪክ ማህበራትን አስፈላጊነት የሚያካትት መሆን ይኖርበታል። በሲቪክ ማህበራት አስፈላጊነት ላይ ግልጽነት ከተጨበጠ በኋላ የሲቪክ ማህበራት መጠናከር (በአካባቢያቸው ከሚያከናውኗቸው ተግባራት አንፃር) ሕዝባዊ ተሳትፎን በማጐልበት ረገድ የሚኖረውን ጠቀሜታ በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል በማቅረብ የጋራ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። |
| • የማህበራቱን ተግባራት | - ሕዝባዊ መነሳሳትን | |

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| ይዘረዝራሉ፣<br>• ለማህበራቱ መጠናከር የህዝብ ንቁ ተሳትፎ መኖር ያለውን አስተዋጽኦ ይገልፃሉ፣ | ለመፍጠር፣<br>- የጋራ አመለካከት እንዲኖር ለማስቻል፣ | |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** በአካባቢ የልማት ዘመቻ ላይ መሳተፍ ያለውን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣ለተሳትፎ የሚያገለግሉ ተቋሞችን ይዘረዝራሉ፣የሲቪክ ማህበራት አደረጃጀትና ዓላማንይዘረዝራሉ፣የማህበራቱን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ለማህበራቱ መጠናከር የህዝብ ንቁ ተሳትፎ መኖር ያለውን አስተዋጽኦ ይዘረዝራሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** በአካባቢ የልማት ዘመቻ ላይ በንቃት ይሳተፋሉ፣ለተሳትፎ የሚያገለግሉ ተቋሞችን ሁኔታ ይገልፃሉ፣የሲቪክ ማህበራት አደረጃጀትና ዓላማን ይገልፃሉ፣የማህበራቱን ተግባራት ይዘረዝራሉ፣ለማህበራቱ መጠናከር የህዝብ ንቁ ተሳትፎ መኖር ያለውን አስተዋጽኦ ይገልፃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።

## 11. ዕውቀትን መሻት

**ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ ፣** **የተመደበው ክፍለ ጊዜ 8**

- ዕውቀት ለልማት፣ ለምርምርና ለፈጠራ መሠረት መሆኑን በመገንዘብ ለትምህርት ያላቸውን ፍላጐት ያሳድጋሉ።
- የመረጃን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ይረዳሉ።
- የመረጃ ምንጮችን፣ የመረጃ አያያዝንና የአጠቃቀም ዘዴዎችን ያውቃሉ።

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| • ተጨባጭና የሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣ | 11.1 ዕውቀት፣ (2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>11.1.1 የሳይንሳዊ ዕውቀቶች ጠቀሜታ፣<br>- ትክክለኛ ውሣኔ ለመወሰን፣<br>- ፈጠራን ለማሳደግ፣<br>- ልማትን ለማፋጠን፣<br>- እራስን ለመቻል፣ | • ለውይይት መነሻ ይሆን ዘንድ ተማሪዎች ሳይንሳዊ ዕውቀቶች የሚባሉት ምን ዓይነት ዕውቀቶች እንደሆኑ እንዲወያዩባቸውና መግባባት ላይ እንዲደርሱ ማድረግ። በመሠረቱ ሳይንሳዊ ዕውቀቶች የሚባሉት በምርምር የተገኙና ማስረጃቸው የማያጠራጥር ዕውቀቶች ናቸው። ለምሳሌ ተማሪ በውጤታማነት እንዲማር ተማሪ ተኮር የሆነ የማስተማር ዘዴ ወሳኝነት አለው። ዕውነታው ይህ ከሆነ ተማሪዎቻችን በጥሩ ሁኔታ እንዲማሩ ምን ዓይነት የማስተማር ዘዴ እንጠቀም የሚለውን ውሳኔ ለመወሰን እንችላለን ማለት ነው። ስለሆነም ለተማሪዎች እንደነዚህ ዓይነት የተለያዩ ጉዳዮችን በማንሳት እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የመረጃ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣<br>• የጥናት ዘዴና የንባብ ልምድን ያሳድጋሉ፣ | 11.2. የመረጃ ምንጮችና አጠቃቀም፣<br>(2 **ክፍለ ጊዜ**)<br>11.2.1 መረጃ ከየት ይገኛል?<br>11.2.2 መረጃ እንዴት ሥራ ላይ ይውላል፣ | • ተማሪዎች የመረጃ አስፈላጊነትን እንዲገልጹ ማድረግ። በአስፈላጊነቱ ላይ ግልጽነት ከተያዘ በኋላ መረጃ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል እንዲያስረዱ ማድረግ። ለምሳሌ የአየር ሁኔታን በተመለከተ መረጃ ከሬዲዮ ሊገኝ ይችላል። መረጃ የሚፈለገው ለመረጃነቱ ሳይሆን አንድ ተግባር ለመፈፀም ነው። ለምሳሌ የአየር ሁኔታን በተመለከተ ከሬዲዮ በሚገኝ መረጃ ላይ ተመሥርቶ ገበሬ እርሻውን በወቅቱ እንዲያርስ ወይ እንዲዘራ ወይ እንዲያጭድ ያደርገዋል። መረጃ እንዴት እንደሚገኝ ተማሪዎቹ በሚያቀ ርቡት ሀሳብ ላይ በመመሥረት መረጃዎቹን እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው በማወያየት የራሳቸውን ዳምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • በአካባቢያቸው የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ | 11.3 ኋላቀር አስተሳሰብና ትምክህተኛ አባባሎች፣ | • በአካባቢያቸው የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ አባባሎችን በቡድን ተከፋፍለው እንዲሰበሰቡ ማድረግ። እነዚህን ያሰባሰቧቸውን አባባሎች ለክፍል ውይይት |

7ኛ ክፍል የሥነዜጋና ሥነምግባር መርሀ ትምህርት

| ከተማሪዎች የሚጠበቁ ብቃቶች | ዋና እና ዝርዝር ይዘቶች | በመምህሩ የሚከናወኑ ተግባራት |
|---|---|---|
| አባባሎችን ይዘረዝራሉ፣ | (2 ክፍለ ጊዜ)<br>11.3.1 በአካባቢ የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ አባባሎች፣ | እንዲያቀርቡና ምን ያህል ጉጂ እንደሆኑ ተማሪዎቹ የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |
| • የተለያዩ መጽሐፍትን ማንበብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣<br>• የአጠናን ዘዴ ያዘጋጃሉ፣ | 11.4 የተለያዩ መጽሐፍትን ማንበብ፣ (2 ክፍለ ጊዜ)<br>11.4.1 የንባብ ልምድን ማበልፀግ፣<br>11.4.2 የትምህርት አጠናን ሥልቶችን መቀየስ፣ | • የሰው ልጅ ዕውቀቱን ሊያዳብር የሚችለው የተለያዩ መጽሐፍትን በማንበብ ነው። የሰው ልጅ መጽሐፍትን ማንበብ ሲያቆም ማወቅ አቆመ ማለት ይቻላል። ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፍትን ማንበብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ እንዲገልጹ ማዳረግ። ትምህርትንም ለማጥናት እንደተገኘ የሚጠና ሳይሆን ለአጠናናችን ዘዴ ወይም ስልት ልንቀይስለት ይገባል። በዚህ ረገድ ካለፈውም ተሞክሯቸው በመነሳት ትምህርታቸውን ለማጥናት ምን ዓይነት ሥልት ሊቀይሱ እንደሚገባቸው በቡድን ተከፋፍለው እንዲወያዩና የራሳቸውን ድምዳሜ እንዲሰጡ ማድረግ። |

## ግምገማ

ተማሪዎች መገምገም ያለባቸው የተለያዩ የመገምገሚያ ስልቶችን በመጠቀም በተከታታይ መሆን አለበት።ግምገማውም ሲካሄድ ከተማሪዎቹ የሚጠበቀውን ብቃትን መሰረት በማድረግና በተማሪዎቹ ላይ የሚታየውን የብቃት ልዩነት በማነፃፀር መሆን ይኖርበታል ።በተጨማሪም መምህሩ የእያንዳንዱን ተማሪ ብቃት በመገምገም ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል።

**ውጤታቸው መካከለኛ የሆኑ ተማሪዎች** ተጨባጭና የሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ጠቀሜታ ይዘረዝራሉ፣የመረጃ አስፈላጊነትን ይገልጻሉ፣የጥናት ዘዴና የንባብ ልምድን ያሳድጋሉ፣በአካባቢያቸው የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ አባባሎችን ይዘረዝራሉ፣የተለያዩ መጽሐፍትን ማንበብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣የአጠናን ዘዴ ያዘጋጃሉ፣

**ውጤታቸው ከፍተኛ የሆኑ ተማሪዎች** ተጨባጭና የሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣የመረጃ አስፈላጊነትን ያብራራሉ፣የጥናት ዘዴና የንባብ ልምድን ያሳድጋሉ፣በአካባቢያቸው የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ አባባሎችን ይዘረዝራሉ፣የተለያዩ መጽሐፍትን ማንበብ የሚሰጠውን ጠቀሜታ ይገልፃሉ፣የአጠናን ዘዴ ያዘጋጃሉ፣

**ውጤታቸው ዝቅተኛ የሆኑ** ተማሪዎችን በመለየት ልዩ ድጋፍና እገዛ በማድረግ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መቀራረብ የሚችሉበትን ሥልት በመንደፍ ውጤታቸውን ማሻሻል ይጠበቃል።